# እግዚአብሔር ሆይ ርዳኝ

እግዚአብሔር ሆይ ርዳኝ ቸርነት አድርገህ (2X)
ዕድሜ ለንስሐ እንደ ሕዝቅያስ ሰጥተህ
ጠማማውን ልቤን በቃልህ አቃንተህ
} አዝማች…

አላውቀውም ብሎ ሲጠየቅ ያመጻው
ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው
የጅረት ወንዝ ነው የሰጠኸው እንባ
ጴጥሮስ ተጸጽቶ ንስሐ እንዲገባ

አዝማች…

ጽዋው እንዳይደርሰኝ የይሁዳ ዕድል
ልጅህ ሆኖ ውሎ ማታ መኮብለል
ጴጥሮስ ዕድለኛ አልቅሶ ተማረ
በትዕቢቱ ይሁዳ እንደወጣ ቀረ

አዝማች…

ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ
ለንስሐ ጠራት ጌታ በገሊላ
ታድሳ ተነሳች በእንባዋ ብዛት
እግሩ ሥር ተደፍታ ማርያም መግደላዊት

አዝማች…

አመጸኛው ልቤ ዛሬስ መቼ ይተኛል
በሐሳብ በዝሙት በስርቆት ይዋኛል
ወደ ቀድሞ ግብሩ እንዳይመለስ
ፍቅርህ በእኔ ሠርጾ ኃጢአቱ ይደምሰስ

አዝማች…

በደላችንን ሁሉ ሳታስብ ትተህ
በምፅአትህ ሰዓት ከጻድቃን ቆጥረህ
ነጭ ልብስ ለብሰን ሆነን ከአንተ ጋራ
በሩ ሳይዘጋ አስገባን አደራ

አዝማች…

# እጠበኝ አምላክ

እጠበኝ አምላክ እነፃለሁ
እጠበኝ ጌታ እነፃለሁ
ኃጢአቴ እንደ አለላ ብትሆንም
ኃጢአቴ እንደ ደም ብትቀላም
እንደ ባዘቶ ትጠራለችና

**አዝማች**

(እጠበኝ አምላክ) የኔን መተላለፍ (እጠበኝ ጌታ) አውቀዋለሁና
»» »» ኃጢአቴም ሁልጊዜ »» »» በፊቴ ነውና

**አዝማች...**

(እጠበኝ አምላክ) የማዳንህን ደስታ (እጠበኝ ጌታ) ጌታ ሆይ ስጠኝ
»» »» በእሽታ መንፈስ »» »» አምላክ ደግፈኝ

**አዝማች...**

(እጠበኝ አምላክ) በሂሶጵ ብትረጨኝ (እጠበኝ ጌታ) እነፃማለሁ
»» »» ከበረዶም ይልቅ »» »» ነጭ እሆናለሁ

**አዝማች...**

(እጠበኝ አምላክ) ሐሴትና ደስታን (እጠበኝ ጌታ) ጌታ ሆይ ስጠኝ
»» »» ምሕረት ይቅርታህ »» »» ዘወትር አይራቀኝ

**አዝማች...**

# ከታገሱት ሁሉም ያልፋል

ኑኃሚን ደጓ ሴት ዛሬስ ምን ሆነሻል
ደስታ ከአንቺ ርቆ ኃዘን ጸንቶብሻል
በሞዓብ ከአገኘሽ ዘይትና ስንዴ
እባክሽ አንቺ ሴት አትጽናኚም እንዴ
ስደተኛ ነኝ ለአገሩ እንግዳ
ለሞዓብ ሰዎች የሆንኩኝ ባዳ
እንባዬ ይፈሳል በዓይኖቼ ሞልቶ
በሰው ሀገር ላይ ወዳጄን አጥቶ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

አይዞሽ እናታችን እጅግ አትከፊ
ይህን የጭንቁን ቀን በጽናት እለፊ
ድንገት እንደዘበት ታሪክ ይለወጣል
የማይተውሽ ንጉሥ ሊረዳሽ ይመጣል
እባካችሁ ተውኝ ሩትና ያርፋ
ዕድለ ቢስ ሆንኩ ኑሮዬም ከፋ
ልጆቼም ራቁኝ ሞት ወሰዳቸው
ናፍቀዋልና ወደ አባታቸው
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

ኑኃሚን ኢትዮጵያ ታላቂቷ ምድር
ስለምን ተሞላሽ ሁከትና ሽብር
የመከራ መሬት ሆነሽ አኬልዳማ
እስከ መቼ ድረስ እንደዚህ እማማ
መራራውን ወይን አስጎንጭቶኛል
መንገዴን ሁሉ በእሾህ አጥሮብኛል
ፍቅርና ሰላም ርቋል ከቤቴ
ያስጨንቀኛል ብቸኝነቴ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

በጊዜው ይሆናል እርሱ የፈቀደው
በስሙ ለሚያምኑት ነገር ለበጎ ነው
የአሕዛብን ሰልፍ ከቅጥርሽ ያግዳል
በቦዔዝ አዝመራ ዳዊት ይወለዳል
ያርግልኝ በእውነት ልጽናና በእርሱ
ልቤን ያበርታው ቅዱስ መንፈሱ
በሰላም ይደር ምስኪኑ ወገኔ
የአገሬን ጥፋት አልየው በዓይኔ
<u>ከታገሱት ሁሉም ያልፋል</u> (2X)
ግን እስኪያልፍ ያለፋል

# ፍቅሩ አይለወጥም

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ
ለስሙ ይሁን ምስጋና } አዝማች…

አልፋና ኦሜጋ ሁሉን የሚገዛ
ዓለም በእጁ ያለች ጥበቡ የበዛ
ሁሉን የምትችል ፈጣሪ ጌታዬ
ሃሌ ሉያ ለአንተ ጋሻ መከታዬ

አዝማች…

ፍቅሩ አይለወጥም ቃሉም አያረጅም
ክብር ለእርሱ ይሁን እስከ ዘለዓለም
እግዚአብሔር ነውና መድኃኒቴ ክብሬ
አወድሰዋለሁ በማቅረብ ዝማሬ

አዝማች…

ሥራው ታላቅና እጅግ ድንቅ ነው
ፍርዱም በቅንነት የተሞላ ነው
መኃሪና ፍጹም ለሆነው ጌታችን
ክብርና ምስጋና ለእርሱ ብቻ ይሁን

አዝማች…

የነገሩትን የማይረሳ ጌታ
የለመኑትንም የማይነሳ ጌታ
ሳይወሰንለት ሰዓትና ቦታ
ምስጋና ይገባዋል ከጧት እስከ ማታ

አዝማች…

ውለታው በዛብኝ ያደረገልኝ
ለመክፈል ባልችልም አመሰግናለሁ
ሃሌ ሉያ ይክበር የእኔ አምላክ መድኅኔ
እያልኩኝ ልጽናና ቆርጫለሁ እኔ

አዝማች…

# አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ

አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ ለብሰህ የማርያምን ሥጋ (2X)
ባክኖ የነበረው የአዳም ዘር ውጤቱ ነበረ የሚያሰጋ (2X)

በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን ድህነትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ (2X)
ምን የበዛ ነበር ትህትናህ ትዕግሥትህ የማይለወጥ (2X)

የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጎንህን ሲወጉህ በጦር (2X)
አንተ ግን ለነርሱ ካባትህ ምህረትን ትለምን ነበር (2X)

ግን መቼ አወቁት እነሱ በኃጢአት ደንድኖ ልባቸው (2X)
መድኃኒታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም ሞትክላቸው (2X)

ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍፃሜ በኋላ (2X)
ኸረ እንዴት እድለኞች ናቸው በፊትህ የሚያገኙት ተድላ (2X)

በዚያች በደብረዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ (2X)
ከቶ ከየት ይሆን ዕጣዬ ያን ጊዜ የኔ አወዳደቅ (2X)

የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ እኔን (2X)
እርዳኝ ፈጣሪዬ ካሁኑ አድሰው የዛገው ልቤን (2X)

# ከመላእክት ጋራ

ከመላእክት ጋራ ሲገለጽ በሰማይ
ጸንተን እንጠብቀው ክብሩን ሁሉ እንድናይ
በግርማ ሲመጣ በአስደንጋጭ ሁኔታ
ወዮልሽ ነፍሴ ሆይ ወየው የዚያን ለታ

ኧኸ. . .
ምስጋና ይድረስህ ሁልጊዜ ጠዋት ማታ
ሃሌ ሃሌ ሉያ የሠራዊት ጌታ (2X) } **አዝማች…**

ሰማይና ምድር ከፊቱ ሲሸሹ
መግቢያ አጥቶ ይጮሃል ትልቁም ትንሹ
ጻድቃን ሲደሰቱ የኃጥአን ፋንታ
ሆኖ ጠበቃቸው ለቅሶና ዋይታ

**አዝማች…**

ስለማይታወቅ አምላክ አመጣጥህ
በመንፈስህ አጽናን ጸንተን እንጠብቅህ
ሠይጣን እንዳይገዛን በመንግሥትህ ቦታ
እግዚኦ ከልለን በመልካሙ ቦታ

**አዝማች…**

ከመላእክት ጋራ ሲገለጽ በሰማይ
ጸንተን እንጠብቀው ክብሩን ሁሉ እንድናይ
በግርማ ሲመጣ በአስደንጋጭ ሁኔታ
ወዮልሽ ነፍሴ ሆይ ወየው የዚያን ለታ

**አዝማች…**

# አንድ ቀን አለ

አንድ ቀን አለ የሚያስፈራ <u>ለጻድቃን የሚያበራ</u> (2X)
ጌታ በዚያ ቀን ይመጣል <u>በክብርም ይገለጻል</u> (2X)

አብረው ከእርሱ ጋር ይመጣሉ <u>ቅዱሳን መላዕክት ሁሉ</u> (2X)
ጌታ በዚያ ቀን ይመጣል <u>በዙፋን ይቀመጣል</u> (2X)

የምሕረት አዋጅ ይጠበቃል <u>ነፍስ ሁሉ ይጨነቃል</u> (2X)
ኃጥአን ሁሉ ያለቅሳሉ <u>በግራው ይቆማሉ</u> (2X)

ቅዱስ ቃሉን ሰምተው ያመኑ <u>የጸኑ በኪዳኑ</u> (2X)
አብረው በቀኝ ይቆማሉ <u>ከኃዘን ይሰወራሉ</u> (2X)

መሐሪ ጌታ ፈጣሪያችን <u>ይድረስህ ልመናችን</u> (2X)
በዚያ ግሩም ቀን እባክህ <u>አቁመን ከቀኝህ</u> (2X)

# ጌታችን ሲመጣ

ጌታችን ሲመጣ በፍርድ ዕለት
ምን ትመልስ ይሆን ወንድም የዚያን ዕለት
ጌታችን ሲመጣ በፍርድ ዕለት
ምን ትመልሽ ይሆን እህት የዚያን ዕለት
} አዝማች...

ጌታችን ሲመጣ በዚያች ክብርት ዕለት
ምን አዘጋጅተናል የምንመልስለት
ለነፍሳችን ግብር መሰብሰብ እንወቅ
በቅዱሳኑ ፊት በፍርድ ሳንጠየቅ

አዝማች...

ጌታችን ሲመጣ ከመላእክት ጋራ
ለመቆም እንድንችል አብረን ከርሱ ጋራ
በተሰበረ ልብ ቀርበን በአንድነት
መጠበቅ አለብን ያችን የፍርድ ዕለት

አዝማች...

ጌታችን ይለያል ስንዴውን ከእንክርዳድ
ዳግመኛ ሲመጣ በዓለም ላይ ሊፈርድ
ፃድቃን ሲደሰቱ የኃጥአን ፋንታ
ሰሚ የሌለው ነው የዚያን ዕለት ዋይታ

አዝማች...

ወንድሞች እህቶች በእምነታችን ፀንተን
የአባቴ ብሩካን እንባል ሁላችን
የመንግሥቱ ወራሽ እንዲያደርገን ጌታ
በጸሎት እንቅረብ በእምነት እንበርታ

አዝማች...

# ኃይልህ ሲገለፅ

ኃይልህ ሲገለፅ በሰማይ (2X)
አቤት! ማን ይቆም ይሆን ከፊትህ
ምን ይቆም ይሆን
ማን ይቆም ይሆን ከፊትህ
ምን ይቆም ይሆን
} አዝማች...

አቤት! ቀንደ መለከት ሲነፋ
አዋጅ ሲታወጅ በይፋ
ፃድቃን ሲጠሩ ለተድላ
ምን ይሆን የእኛ ተስፋ

አዝማች...

አቤት! መላእክት ሰማዩን ሲያርሱት
ቀድሞ ሲሰሙ መባርክት
ያልታየና ያልተሰማ
ድምፅ ሲሰማ ከራማ

አዝማች...

አቤት! ሰባቱ ንፋስ ተከፍተው
ምድርን ሲያውኳት ቀስፈው
ሲታዘዝ የባሕር ሞገድ
ምድሪቱን ሊከድናት ለፍርድ

አዝማች...

አቤት! ሲጠሩ ፃድቃን ቅዱሳን
መልካም የሰሩ ብሩካን
በምድር የሰሩትን ትሩፋት
ሲያቀርቡ ለአምላክ ስብሃት

አዝማች...

አቤት! ኃጥአን ሌት ለፍርድ ሲጠሩ
በጨለማ ዓለም ሊቀሩ
የማይጠቅም ዋይታ ሆኖ
መዋረድ ይሆናል አዝኖ

አዝማች...

አቤት! ሲጠሩ ፃድቃን ቅዱሳን
መልካም የሰሩ ብሩካን
በምድር የሰሩትን ትሩፋት
ሲያቀርቡ ለአምላክ ስብሃት

አዝማች...

# እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው } አዝማች...

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሦብን ሳለ በኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራው ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው (2X)

አዝማች...

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
እንደምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት (2X)

አዝማች...

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

አዝማች...

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

አዝማች...

# ድንግል ሆይ እመቤቴ

የብርሃን ደጃፍ ያደረብሽ ጌታ
ፈጥነሽ ድረሽልኝ ካለሁበት ቦታ
ሐዘኔ ቢበዛ ብወድቅ በኃጢአት
ታማልደኛለች ድንግል ከእኔ ጋር ናት

ድንግል ሆይ እመቤቴ የአምላክ እናት
ስደክም ሲያገኘኝ መከራ ሁኚኝ ረዳት } **አዝማች...**

ጭንቀቴ ቢበዛ የሚያጽናና አጥቼ
ሕይወቴም ቢሸበር ሰላም ተነስቼ
ኃጢአት ቢፈትነኝ ተሸናፊም ብሆን
አማላጅ አለችኝ ለእኔ የምትለምን

**አዝማች...**

ደስታዬ ርቆ ቢበዛ ኃዘኔ
ድንግል ሆይ አስታርቂኝ ለምኚ ስለ እኔ
የኃጢአት ብዛት ሲያቆስለው መንፈሴን
ከጌታ ከልጅሽ አሰጪኝ ምሕረትን

**አዝማች...**

ስምሽ ከሚነሳ በክፉ ነገር
እኔ ኃጢአተኛው ልወጋ በጦር
ከአዳም ልጆች ሁሉ ተመርጠሻልና
ለአንቺ ይገባሻል ክብርና ምስጋና

**አዝማች...**

# አበረታኝ ፍቅርህ

አበረታኝ ፍቅርህ ጌታዬ
አበረታኝ ክንድህ አምላኬ
በስምህ ድኛለሁ በጸጋህ
በማደሪያህ ሆኜ ስጠራህ

**አዝማች...**

ሰዶም ስትቃጠል መርገሟ ሲበዛ
ሊተወኝ አይሻም ልጁን እንደዋዛ
ሕጉን በማሰቤ አምላክ ፈረደልኝ
ጎትቶ የሚያወጣ መልአክ ሰደደልኝ

**አዝማች...**

በገናን መደርደር አያቆምም ጣቴ
የወንጭፌ ድንጋይ አንተ ነህ ጉልበቴ
የሳኦልን ካባ አውልቀህ ጣልክልኝ
የፍልስጤሙን ሰው ክንድህ ሰበረልኝ

**አዝማች...**

ሦስት ጊዜ ስክድህ አላውቅህም ብዬ
ዶሮ ስለጮኸ ትዝ አልከኝ ጌታዬ
ወጣሁኝ በእንባ ከአይሁድ እሳት ሥር
ከሃዲ ሳትለኝ አኖርከኝ በፍቅር

**አዝማች...**

ሳምራዊት ናት ሳትል ክብርን የሰጠኸኝ
እንደ አንተ ከአይሁድ ፍቅርን ማን አሳየኝ
ሚስጥሬን በሙሉ ነገርከኝ ጌታዬ
የፍቅር ውሃ ቀዳሁ እንሥራዬን ጥዬ

**አዝማች...**

# እግዚአብሔርን ጠራሁት

እግዚአብሔርን ጠራሁት በኃዘኔ ጊዜ
እግዚአብሔርን ጠራሁት በጭንቀቴ ጊዜ
አወጣኝ ከጭንቀት ከኃዘን ከትካዜ (2X) } **አዝማች** (2X)

የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና
ጆሮውን ወደእኔ አዘንብሏልና
በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለሁ
ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና አቀርባለሁ } (2X)

**አዝማች**…

እንደቃልህ መጓዝ መራመድ አቅቶኝ
የኃጢአቱ ሞገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ
ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞም ስጸጸት
አላሳፈረኝም መጣ በምሳረት } (2X)

**አዝማች**…

በገዛ ምሳረቱ ያለፈውን ትቶ
በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ
ሊቀበለኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ
ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ } (2X)

**አዝማች**…

ኖሕን እንዳዳንከው እኛንም አድነን
ከቀስቱ እንድናመልጥ ምልክትን ስጠን
በትርህ ምርኩዝህ እነርሱ ያፅናኑኝ
አንተ ከእኔ ጋር ነህ አልፈራም ክፉውን } (2X)

**አዝማች**… (2X)

# ከደጅህ ቆሜ

ከደጅህ ቆሜ እንኳኳለሁ
ድምፄን ብትሰማ እገባለሁ
ከአንተም ጋር ራት እበላለሁ
በዚያ ያሉትንም እባርካለሁ } አዝማች...

በራድ ወይም ትኩስ ብትሆን መልካም ነበር
እንዲያው ለብ ስላልክ ከንቱ የአንተ ነገር
አሁኑኑ ምረጥ ቦታህን አደላድል
ሥጋህንም መርጠህ ደግመህ እንዳትጣል

አዝማች...

ሀብታም ባለጸጋ ሆኛለሁኝና
አያስፈልገኝም ሁሉም አለኝና
ጎስቋላና ምስኪን መሆንህን የማታውቅ
በደከመ ሕይወት ያለህ የምትዋዥቅ

አዝማች...

በእሳት የነጠረ ወርቅን ተጎናጽፈህ
ሀፍረት እንዳይመጣ ነጭ ልብስን ለብሰህ
የምትኳለውን ኩሉን ከእኔ ገዝተህ
ሁሉንም አስተውል ልቦናህን ገልፀህ

አዝማች...

የምወዳቸውን እገስጻቸዋለሁ
የእኔ የሆኑትን እቆጣቸዋለሁ
እንግዲህ ቅና ንስሐ ግባና
አዲስ ሰው ሁን ልጄ ዛሬም እንደገና

አዝማች...

# ስምሽ ይጣፍጣል

ስምሽ ይጣፍጣል ከማር ከወተት
ቤዛዊተ ኩሉ የሁሉ እመቤት
የዓለምን መድኅን ወለድሽው
የፍጥረታት አማላጅ የሆንሽው (2X) } አዝማች...

እጅ መንሳቴንም ተቀበይልኝ
ስምሽን ስጠራ ወዴት ነህ በይኝ
አፌ ተናገረ ድንግል ክብርሽን
አዘክሪ ድንግል ቃል ኪዳንሽን
አፌ ተናገረ ድንግል ክብርሽን
አዘክሪ እናቴ ቃል ኪዳንሽን

አዝማች...

አብ የተከለሽ ነሽ ወይኑን ያፈራሽ
ዓለም ተፈወሰ በመድኅን ልጅሽ
ቁስሌ ደረቀ ተለወጠ ሞቴ
ሰላም ልበልሽ ድንግል እመቤቴ (2X)

አዝማች...

ሲዘጋ በሔዋን በአንቺ ተከፈተ
ተረታ ጠላቴ ልቤም ተደሰተ
መዳኔን ሰማሁ ያን አዋጅ
እጅ እነሣለሁ ከአንቺ ደጅ (2X)

አዝማች...

ስወጣ ስገባ ሰላም ለኪ ብዬ
ውዳሴሽ ጣፈጠኝ ድንግል አለኝታዬ
ሰማይ ብራና ቢሆን እንኳ
ድንግል ሆይ ክብርሽ አይለካ (2X)

አዝማች...

# ሞተሃልና ስለኔ

ሞተሃልና ስለኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከሰህ ተወቅሰህ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አምላከ ምሕረት (ስብሐት ለከ)

የአንተ መንገላታት ሁል ጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ
በመስቀል ላይ ሆነህ ያየኸው መከራ
ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ (ስብሐት ለከ)

ከልዑል ቦታ ወርደህ ፈጣሪ የፍጡራን አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለሰው የሞትክ
በመስቀል ላይ ተጠማሁ እያልክ (ስብሐት ለከ)

ክፉ አድራጊዎች ተነስተው በምቀኝነት መንፈስ
ብዙ ሲጣጣሩ ለደምህ መፍሰስ
ሞትክላቸው እንዲላቸው ደስ (ስብሐት ለከ)

መሐሪ ጌታ አሁንም እንደቸርነትህ ብዛት
የእኛን በደል ሁሉ ሳትመለከት
አድነን ከዳግም ሞት (ስብሐት ለከ)

# በመስቀል ተሰቅሎ

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለፀው
ምን ስጦታ አለን ለሱ የምንከፍለው
ምስጋና ነውና ከኛ የሚፈልገው
ቸሩ አምላካችንን ተመስገን እንበለው } **አዝማች...**

ዓለም እሰኪደነቅ ድንቅ አድርጎልናል
እንዲሁ ያለ ዋጋ ፀጋውን ሰጥቶናል
ትናንት ለእሥራኤል ሞገስ የሆናቸው
ስሙን እናመስግን ዛሬም ከእኛ ጋር ነው

**አዝማች...**

አፋችን ይሞላ በታላቅ ምስጋና
ከኃጢአቱ ባሕር ተሻግረናልና
ክቡር ምስጉን አምላክ ቅዱስ እንበለው
ኢሳይያስም በክብር በራዕይ እንዳየው

**አዝማች...**

ከቶስ ለእግዚአብሔር ምን ይከፈለዋል
ሁሉም የራሱ ነው ማን ምን ይሰጠዋል
አመስጋኝም ቢሆን ክብር ለራሱ ነው
እሱ በባሕሪው ዘላለም ምስጉን ነው

**አዝማች...**

ሙሴም ዝም አላለ ዳዊትም አልተኛ
በጎቹም ዘመሩ ለመልካሙ እረኛ
ያሬድ ተመሰጠ ወደ ሰማይ ዓለም
እኛም ከነሱ ጋር እንዘምር ዘላለም

**አዝማች...**

# ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ (3X) ምስጋና በሰማይ በምድር
ሰውን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር
ምስጋና በሰማይ በምድር
እኛን ለወደደን ለእግዚአብሔር
} **አዝማች...**

ይህን ልዩ ፍቅር እዩ ተመልከቱ
ልጆቼ ብሎናል የሰማይ አባቱ
ወዶናል በነፃ አንድ ልጁን ሰጥቶ
አብን እናመስግን አፋችን ተከፍቶ

**አዝማች...**

በሥጋ ተገልጦ አየነው ዳሰስነው
እስከ መስቀል ድረስ በፍቅር የታዘዘው
ወልድን አይተነዋል አምነናል በስሙ
አለ በላያችን ደመ ማኅተሙ

**አዝማች...**

አንድም ሦስትም ሆኖ አለ ሲጠብቀን
ለዘለዓለም ጥፋት አይፈቅድም ሊሰጠን
ለእኛ ያለፈውን የፍቅሩን ብዛት
እያየን አድገናል ሳንፈራ ሞት

**አዝማች...**

በነገሥታት መንደር ቢነሳብን ቁጣ
ስለእኛ ሊናገር መንፈስ ቅዱስ መጣ
ቤተ ክርስቲያንን በእሣት አከበረ
እንዳንፈራ ሆነ ድካማችን ቀረ

**አዝማች...**

ግርማዊ መንግሥቱ ምጡቅ ብትሆንም
ምስጋናና ቅኔ ከአፋችን አይጎድልም
ታምኗል በፊታችን እንከን ሳይኖርበት
ለረዳን እግዚአብሔር እልል እንበልለት

**አዝማች...**

# የወርቅ መሰላል ነሽ

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ
መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ
ሰውና አምላክን ያገናኘሽ
} **አዝማች** (2X)

አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ (2X)
አሸልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጤዛ
ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ መሰላል
ምሳሌሽን አየ ማርያም ድንግል

**አዝማች**...

መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ (2X)
እንደ አየ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ
ተሰፋ አድርጎ ሲኖር የሰላሙን ዘመን
ይኸው ተፈፀመ በአንቺ በእናታችን

**አዝማች**...

በአንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም (2X)
በአንቺ ተፈፀመ የያዕቆብ ህልም
ሰውና መላእክት ተለያየተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድነት ዘመሩ

**አዝማች**... (2X)